*አጭር ጽሑፍ፡-*

*ጉዞዎን ጤናማ ያድርጉ*

*ወንድ ልጇ ክትባት መከተብ ነበረበት፤ በመጨረሻም እንቅልፍ ይዟት ሄደ። ቤተሰባቸውን ለመጠየቅ ወደ ኬንያ ስለሚሄዱ ሁኔታው የተለየ እንደሆነ እና ልጇ ከተለመደው ግዜ አስቀድሞ ክትባቱን መከተብ እንዳለባት ዶክተሩ ማሳሰቢያቸውን ሰጥተዋል። ተመልሰው እስኪመጡ ድረስ ሊቆይ እንደሚችል ወሰናች። ጉዞውን የሚያርጉት ቤተሰብ ለመጠየቅ በመሆኑ ከባድ አደጋን የሚያስከትል አይመስልም ነበር።*

*ወደ ቤታቸው በተመለሱበት ቀን ልጇ የጉንፋን በሽታ ምልክቶች ይታዩበት ነበር – ሳል፣ ከአፍንጫ ላይ ያለማቋረጥ የሚወርድ ፈሳሽ ወይም ንፍጥ፣ እንባማዘል እና የአይን መቅላት የታዩት የህመም ምልክቶች ናቸው። ከዚያም በሰውነቱ ላይ ከፍተኛ ሙቀት ከተፈጠረ በኋላ በድካም ስሜት ተዝለፈለፈ። የሳሉና የሰውነቱ የሙቀት መጠን በጣም እየጨመረ በመሄዱ እንደገና ወደ ዶክተር ይዛው ስትሄድ ህመሙ በቫይረስ ምክንያት እንደተከሰተና የቅርብ ክትትል እንደሚያስፈልገው ተነገራት። ያኔ በተደረገለት የጤና ምርመራ ኒሞኒያ ወይም የሳንባ ምች በሽታ እንዳለበት ስለተረጋገጠ ሆስፒታል ውስጥ እንዲተኛ ተደረገ። ዶክተሮቹ ተጨማሪ ምርመራዎችን ካደረጉለት በኋላ ህጻኑ ልጅ የኩፍኝ በሽታ እንደያዘው ስለተረጋገጠ ለብቻው በአንድ ክፍል ውስጥ እንዲተኛ ተደረገ።*

*ልጇ መተንፈስ ስለተቸገረ የመተንፈሻ ማሽን ላይ እንዲሆንና እርዳታ እንዲያገኝ አደረጉት። በአፉ፣ በአፍንጫው እና በክንዶቹ ላይ የተለያዩ ቱቦዎች ተሰክተው ይታዩ ነበር። እናት ልጇን ለይታ ማወቅ የማትችልበት ደረጃ ላይ ደርሳ ነበር። የተስፋ መቁረጥ ስሜት ውስጧን ሲወራት ተሰማት። ዶክተሮቹ ልጇ ሊሞት እንደሚችል ስጋታቸውን አሳወቋት። ለሶስት ሳምንት ያክል ልጇ በማሽን እርዳታ እየተነፈ ለመቆየት ቻለ። ህጻኑ ልጅ ከሞት ለጥቂት ቢያመልጥም እንቱ ግን ልጇ ያሳለፈውን የስቃይ ግዜ በጭራሽ የምትረሳው አትመስልም። ወደ ውጭ ሀገር የሚጓዝ ማንኛውንም ሰው ስታገኝ "ለእርስዎም ሆነ ለቤተሰብዎ አባላት አስፈላጊውን ሁሉ ክትባት መከተባችሁን እርግጠኛ መሆን አለባችሁ" የሚል ምክሯን ከመለገስ ወደ ኋላ አትልም።*

*ይህ እንዴት ሊከሰት ቻለ? በእንግድነት በቆዩበት ቤት ውስጥ የታመመ ሰው አልነበረም እንዲሁም ልጇን ወደ ሱቅ ወይም ሌላ ቤተሰብን ለመጠየቅ ስትሄድ ካልሆነ በስተቀር ልጇን ወደ ውጭ ይዛ ትወጣ የነበረው ከስንት አንዴ ነበር። የኩፍኝ በሽታ የሚያስከትለው ችግር የቆዳ ማሳከክን ብቻ ነውን? ኩፍኝ በልጇ ላይ ከፍተኛ የህመም ስሜትን ሊፈጥር የቻለው እንዴት ነው?*

*ኩፍኝ በመላው ዓለም በየቀኑ 430 ህጻናትን ለሞት የሚዳርግ በሽታ ነው። በከፍተኛ ደረጃ የመተላለፍ ባህሪ ያለውና ክትባቱን ያልወሰዱ ህጻናትን በፍጥነት የሚያጠቃ በሽታ ነው። ከአንዱ አህጉር ወደ ሌላ አህጉር በቀላሉ ይዛመታል። በዚህ ታሪክ ውስጥ የተጠቀሰው ህጻን ልጅ በተጓዘበት አውሮፕላን ውስጥና ወደ ሚኒሶታ ሲመለስ ከቤተሰቡ አባላት መካከል ክትባቱን ወዳልተከተቡ ሌሎች ህጻናት በሽታውን አስተላልፏል። ወደ ውጭ ሃገር የሚጓዙ ከሆኑ እርስዎና ልጆችዎ ወቅታዊ የሆኑ የኩፍኝ፣ የመምፐስ እና የሩቤላ ክትባትን (MMR ተብሎ የሚጠራ) የመሳሰሉ ክትባቶችን መከተባችሁን እርግጠኛ መሆን አለባችሁ። እድሜያቸው እስከ 6 ወር ድረስ የሆናቸው ህጻናት የሩቤላ ወይም MMR ክትባትን መከተብ አለባቸው።*

*ፖሊዮ በመንገደኞች አማካኝነት ከአንዱ አገር ወደ ሌላው አገር የሚዛመት ሌላ ተላላፊ በሽታ ነው። ፖሊዮ አንድን የሰውነት ክፍል ሽባ የሚያደርግ (እግር ወይም ክንድ መንቀሳቀስ እንዳይችል የሚያደርግ) እና አንዳንዴም የማጅራት ገትር በሽታን (በጭንቅላትና በህብለ ሰረሰር ላይ የሚያጋጥም ህመምን) የሚያስከትል በሽታ ነው። ሽባነቱ እየተስፋፋ ከሄደ በበሽታው የተጠቃው ሰው መተንፈስ ሊያቆም ይችላል። የፖሊዮ በሽታ መዛመት በዓለም የጤና ድርጅት ውስጥ ያሉ የጤና ጉዳይ ባለስልጣናትን እጅጉን የሚያሳስብ ጉዳይ ነው። ፖሊዮ በሚገኝበት አገር ውስጥ ከአራት ሳምንት በላይ የቆዩ ሰዎች ወደ አገራቸው ከመመለሳቸው በፊት*

ክትባቱን መከተብ እንዳለባቸው ምክራቸውንና ማሳሰቢያቸውን ይሰጣሉ። የፖሊዮ በሽታ ወደተገኘባቸው አገራት የሚጓዙ ሰዎች ለራሳቸው በሽታዎቹን የመከላከል አቅማቸውን ማሳደግ እንዲሁም ህጻናት ልጆቻቸው ለጉዞው የሚያስፈልጋቸውን ሁሉንም ክትባቶችንና መድኃኒቶችን መውሰድ የሚያስፈልግ እንደሆነ የህክምና ክሊኒካቸውን ማማከር አለባቸው።

በሚያደርጓቸው ጉዞዎች ጤንነትዎን ለመጠበቅ ስለሚያደርጉት ጉዞ፣ ስለሚያስፈልግዎት ክትባቶች እና በጉዞዎ ወቅት ጤንነትዎን ስለሚጠብቁባቸው መንገዶች ከክሊኒክዎ ጋር ይነጋገሩ። አንዳንዴ በጉዞ ምክንያት የህመም ስሜት ይፈጠራል። እርስዎና ቤተሰብዎ ከዓለም አቀፍ ጉዞ ወደ ቤትዎ ሲመለሱ የህክምና ክትትል ወደሚያደርጉበት ክሊኒክ በመደወል የሚታዩብዎትን የህመም ምልክቶችንና በቅርቡ ጉዞ አድርገው እንደነበር ያሳውቋቸው።